# መጽሐፍ ቅዱስ

በባህርዩ ንጹሕ ቅዱስ ሆኖ ሳለ ከሰዎች ጋር ለመወያየት ራሱን ትሑት ያደረገው አምላካችን ቡሩክ ነው። ሰው ሁሉ ለመንገዱ ብርሃን ይሆንለት ዘንድ ነፍስም ሕይወት አግኝታ እንድትኖርበት ነቢያቱን ያናገረ፣ የተናገሩትንም እንዲጽፉት ያዘዘ ፈጣሪያችን ቅዱስ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ «የመጻሕፍት መጽሐፍ» እውነትም «ታላቅ መጽሐፍ» ነው። መጽሐፍ ሲባልም የእግዚአብሔር መጽሐፍ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው። በእርሱ አንተን ይናገርበታል። መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ የተገለጸና በቅዱሳን ነቢያት እና ሐዋርያት አንደበት የተነገረ እውነት ነው። «ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፣ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።» (2ጴጥ. 1:21) ጥቅሙም እንድትማርበት፣ ለእግዚአብሔር የቀና ልብ እንዲኖርህ፣ በአጠቃላይ የፈጣሪህን ፈቃድ ተከታይ እንድትሆን ለማድረግ ነው። (2 ጢሞ 3:16)።

መጽሐፍ ቅዱስ ለአንተ ከእግዚአብሔር የተላለፈልህ መልእክት ነው።

በዚህ ከአምላኩ ከእግዚአብሔር በመጣለት መልእክት ደስ የማይለው ማነው? በአንድ ወቅት ታላቁ ቅዱስ አባት አባ እንጦንስ ከንጉሥ ቆስጠንጢኖስ የተላከ ደብዳቤ ደረሰው። ደቀ መዛሙርቱም አባታቸው የንጉሥ ደብዳቤ ስለደረሰው እጅግ በጣም ተደሰቱ። እርሱ ግን ምንም የተለየ ግምት ሳይሰጠው ወደጎን አለው። አሁንም ተማሪዎቹ ከመደነቅ ብዛት ለማንበብ በጣም ጓጉ። አባ እንጦንስ ግን «ልጆቼ ከሰው ለመጣ ደብዳቤ እንዴት እንደዚህ ደስ ይላችኋል? እነሆ የነገሥታት ንጉሥ እግዚአብሔር የብዙ ብዙ ደብዳቤዎችን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ልኮልናል። ለምን በዚህ መልእክት እንደዚህ አትደሰቱም? ለማንበብስ እንዴት አያጓጓችሁም? ብሎ



www.ethiopianorthodox.org

ስለመጽሐፍ ቅዱስ ካስተማራቸው በኋላ ደብዳቤውን አነበበ። ለንጉሡም የሚያስፈልገውን የበረከት መልስ ሰጠው።

አንተስ ከምትወደውና ከምትናፍቀው ሰው ደብዳቤ ቢደርስህ እጅግ ተደስተህ በየሰዓቱ ታነበው የለም? ከሆነ ደግሞ ከእግዚአብሔር ለመጣልህስ ይህን ያህልና የበለጠ መደሰትና መጓጓት በየሰዓቱ ማንበብ አይገባህም ነበር? ይህ ከእግዚአብሔር ወደአንተ የተላከው መልእክት በመንፈስ ቅዱስ የተቃኘ፣ ይመራቸው በነበሩ ነቢያት የተነገረ እና ቃሉ ራሱ በመንፈስ ቅዱስ የሆነ መልእክት ነው። ይህን ደግሞ በውስጡ ባለው መንፈስና ሕይወት መረዳት ትችላለህ። ጌታችንም «እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው፣ ሕይወትም ነው።» ሲል ተናግሯል (ዮሐ. 6፡63)

መጽሐፍ ቅዱስ ተመግበኸው ሕይወት እንድታገኝበት ከእግዚአብሔር የተሰጠህ መንፈሳዊ ምግብ ነው። ጌታችን ዲያብሎስ ሊፈትነው በቀረበ ጊዜ ከመጽሐፍ ቅዱስ (ዘጸ. 8:3) ጠቅሶ እንደተናገረው ሰው ከእግዚአብሔር በሚወጣው ቃል ጭምር እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም። (ማቴ 4:4) ለሥጋዊ ሕይወትህ የሚሆን ሥጋዊ ምግብ አለህ። ነገር ግን አንተ ሥጋ ብቻ አይደለህም። በውስጥህ የማይሞት የማይበሰብስ መንፈስ አለ። ስለዚህ መንፈሳዊውንም ምግብ መጽሐፍ ቅዱስን ተመግበህ ሕይወት ማግኘት አለብህ «እውነት እውነት እላችኋለሁ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው....» (ዮሐ. 5:24) ።

ወንድሜ ሆይ! መኖር የምትችለው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባለው የሕይወት ቃል ጭምር እንጂ በእንጀራ ብቻ እንዳልሆነ እርግጠኛ ሁን። «ዛሬ የዕለት ምግባችንን ስጠን» እያልክ ስትጸልይም የሕይወት ምግብህንም የሚያጠቃልል እንደሆነና ስለሥጋህ ብቻ እንደማትጠይቅ ልብ በል። የእግዚአብሔር ሰው ሆይ የአንተ ደስታ መሆን ያለበት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው። (መዝ 1:2) ሌት ተቀንም አስበው። ደስታህም የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ሕግ የሚያስጨንቅ ግዴታ ሳይሆን የሕይወት ምንጭ መሆኑን መረዳትህን ነው።



መጽሐፍ ቅዱስና የእግዚአብሔር ሰው ያላቸው ግንኙነት ቋሚና የማያቋርጥ ነው፣ ሕጉን በቀንም በሌሊት ያስባል። ይህን ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ የሚሠራ አነጋገር አድርገህ አትውሰደው። የአንተም የሌላውም የሁላችንም ነው።

የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንዲመራ ለተጠራው፣ ለሙሴ ተከታይ፣ ለነዌ ልጅ ኢያሱ በዚያ ሁሉ ሕዝብ አመራር ኃላፊነት ውስጥ ሆኖ ሳለ እግዚአብሔር የነገረውን ቃል አስተውል። «የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፣ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌትም አስበው። የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል፣ ይከናወንልሃል (ኢያ 1:8) ። እንግዲህ ያን ሁሉ ሕዝብ የመምራት ኃላፊነት ለነበረበት ሰው እግዚአብሔር «የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ» ሲለው አንተ ምን ታስባለህ? ይህንንም ለኢያሱ ብቻ ሳይሆን ለእኔም ለአንተም እንደሆነ እመን። ለዚህም ነው መዝሙረኛው ቅዱስ ዳዊት የእግዚአብሔር ሰው ደስታ በእግዚአብሔር ሕግ፣ እርሱንም ሌት ተቀን በማሰብ እንደሆነ በመዝሙሩ መጀመሪያ ላይ የተናገረው።

እርሱ ራሱ ንጉሥ ዳዊትም መሪና ንጉሥ፣ የኃላፊነት ሰው ሆኖ ሳለ «ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴም ብርሃን ነው» አለ። (መዝ 118:105) እንዲሁም፣ የእግዚአብሔር ቃል ከማር ከሦከር ይልቅ ለእኔ ይጥመኛል አለ።

ንጉሥ ዳዊት እንዴት ሕጉን በቀንና በሌሊት የማሰቢያ ጊዜ አገኘ? አንተስ እንዴት አጣህ? አባቶቻችን ቅዱሳን መጽሐፍ ቅዱስን ከልባቸው በፍቅር ይማሩት ስለነበረ በሕይወታቸው ሙሉ መጽሐፉ የተገለጠ ነበር። አንተም የእግዚአብሔርን ቃል እያወቅህ እየተማርክ በሄድክ ቁጥር በሌትም በቀንም እያሰብከው ትመጣለህ። መጽሐፍ ቅዱስን አንተ ተማረው፣ እርሱም ይጠብቅሃል። በቤትህ፣ በሥራህ፣ በመንገድህ፣ በሰዎች መካከል ሆነህ አስበው፣ ወዳጅህ አድርገው። አንተ የቃሉ ወዳጅ ስትሆን የቃሉ ባለቤት እግዚአብሔር ደግሞ የልብ ወዳጅህ ይሆናል።



www.ethiopianorthodox.org

ቃሉን ደጋግመህ አጥናው፣ ሁሌም አትርሳው። ይህ ከበጎ ምግባር ሁሉ የመጀመሪያው ነውና።

ይህን በተመለከተ አምላክህ የሚናገርህ አለው። «ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል» ማቴ 7፡ 24። በጸሎተ ቅዳሴያችንም ላይ ካህኑ «ቅዱስ የሆነ የወንጌልህን ቃል እንድንሰማና፣ እንደሰማንም እንድንሠራ በቅዱሳን ጸሎት የበቃን የተዘጋጀን አድርገን» ይላል። «የበቃን» ሲል ጥልቅ የሆነ ትርጉም አለው። ለሕጉ ለትእዛዙ ያልታመንን እኔና አንተ ቅዱስ የሆነውን የወንጌሉን ቃል ለመስማት እኛ ማንን? «የበቃን» ያደረገን፣ የሕይወትን መጽሐፍ ወደእርሱ የምንጓዝበት መንገድ አድርጎ የሠጠን አምላካችን ነውና፣ እርሱን «የበቃን» አድርገን ብለን፣ እንደፈቃዱ በኖሩት፣ ቃሉን በተማገቡት በቅዱሳኑ ስም እንለምነዋለን።

የእግዚአብሔር ሰው ክርስቲያን ሆይ! እጅግ ብዙ የተጠቀምክበትና፣ ብዙ ነገር የምታስታውስበት መጽሐፍ ቅዱስ በእጅህ ላይ ሊታይ ያስፈልጋል። ለእይታ ለጌጥ ብቻ ያልሆኑ፣ ብዙ የተነበቡ፣ የዘወትር አማካሪ የሆኑ መጻሕፍት የክርስቲያን መለያዎች ናቸው።

እባክህ ይህን የሕይወት መጽሐፍ ተጠቀምበት።

አንብበው፣ አስበው። ወደጥልቁ ዕውቀት ግባና ከነፍስህ ጋር አዋህደው። ቃል በቃል በሚሠጥህ ትርጉም ብቻ ተመስርተህ ባገኘኸው ነገር ደስ አይበልህ። ጠልቀህ ስታስብ አንዱን ቃል የውቅያኖስ ያህል እጅግ ሠፊ ሆኖ ታገኘዋለህ። ቅዱስ ዳዊት እንደተናገረው ወሰን የሌለው ድንቅ ምሥጢር የሚገኝበት የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው። «የሥራን ሁሉ ፍጻሜ አየሁ፣ ትእዛዝህ ግን እጅግ ሠፊ ነው።» (መዝ 118፡96)

ዳዊት ይህን የተናገረበት ጊዜ ገና ዘጠኝ የሚያህሉ መጻሕፍት የነበሩበት ነው። ዛሬ አንተ ሙሉ የሆነ፣ ነቢያትን፣ አዲስ ኪዳንን ያጠቃለለ መጽሐፍ ቅዱስ ከነትውፊቱ አለህ።

እያንዳንዱ ቃል የእግዚአብሔር ነውና ጥልቅነቱን ሥፋቱን አስብና፣ የተሰጠህን ሀብት የመጽሐፉን ምንነት በደንብ ተረዳ።

መጽሐፍ ቅዱስ የሐሳብ ምንጭ ብቻ ሳይሆን መጽናኛም ነው። ዛሬ ላለህበት የትኛውም የሥነ አእምሮ፣ የሥነ ልቡና ሁከት እና ረሃብ መጽሐፍ ቅዱስ እንድትጽናናበት፣ እንድትረካበት የሚያደርጉህ ቃላት ይገኙበታል። ያዘነ፣ የተከዘ ሰው ቢኖር የሚፅናናበትና ደስ እንዲለው የሚያደርግ፣ የተረበሸም ሰው ሰላሙን የሚመልስለት ቃል የሚገኝበት መጽሐፍ ነው። ለአንተም በመከራህ ሰዓት መፍትሔን፣ ሰላም ባጣህበት ጊዜ የውስጥ ሰላምን ተስፋ ብትቆጥ የሚያበራ የተስፋ ብርሃት ቃልን የምታገኝበት ድንቅ ሥጦታህ ነው። ቃላቱ ሁሉ የሚለውጡህና ውጤታማ ናቸው። እያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ባነበብክ ቁጥር «አምላኬ ሆይ ይህን ስለኔ እንደተናገርከ ጥርጥር የለኝም» በለው። በግል ለአንተ ከእግዚአብሔር የመጣ መልእክት አድርገህ ተቀበለው።

እግዚአብሔር ስለአንተ ነቢያቱን አናገረ። መልእክታትም ለቆሮንቶስና ለሮሜ ክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆን ለአንተም ተላኩ። ቅዱስ አባት እንጦንስ የንጉሥ ቆንጠንጢኖስ ደብዳቤ ሲደርሰው ደቀ መዛሙርቱ ምን ያህል ተደስተው እንደነበረ እና እንዴት አስተምሮ እንዳሳመናቸው አስታውስ። የነገሥታት ንጉሥ፣ የእግዚአብሔር መልእክት እነሆ ለአንተ ደርሶሃል። ስለምን በእርሱ ደስ አይልህም?

የመጽሐፍ ቅዱሳችን ቃል መጽናኛ ብቻ ሳይሆን የጦር መሳሪያም ነው። ለእያንዳንዱ ኃጢአት በፊቱ የሚቀመጥ «አታድርግ» የሚል ሕግ አለ። በዚህ ምክንያት ከሕገ እግዚአብሔር ካገኘሽው ቃል የተነሳ ኃጢአትን ደካማ ሆኖ ታገኘዋለህ የእግዚአብሔር ቃል ምን ያህል ጠንካራ እንደሆነና በኃይል እንደሚሠራ ታውቃለህ? «የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፣ የሚሠራም ሁለትም አፍ ካለው ሠይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፣ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፣ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል» (ዕብ 4፡12)



www.ethiopianorthodox.org

ሰይጣን ፈታኝ ሆኖ በቀረበበት በዚያ ተራራ ላይ የእግዚአብሔርን ቃል ሊቋቋመው አልቻለም፤ ያገኘለትም ምላሽ አልነበረም። (ማቴ.4:1-11)

የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተህ የማትሠራበት ከሆነ፤ በመጨረሻው ቀን በአንተ ላይ ይፈርዳል። ቃሉ ለዕውቀት ብቻ ሳይሆን ለሕይወት ነው። በሄድክበት የሚሄድ፣ ዘወትር በጆሮችህ የሚያቃጭል እና በተግባር ካላዋልከው ከባድ የሕሊና ወቀሳን የሚያስከትል ነው። በአንጻሩ ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል በአንደበትህ፣ በንግግርህ፣ ሁሉ ካለና በተግባርህ የሚገለጥ ከሆነ ለመንፈሳዊነትህና ለሃይማኖትህ ታማኝ እንደሆንክ ይመሰክራል። ዓለማዊ ነገሮችን ብቻ የሚያወሩ ብዙ ሰዎች አሉ። እንደዚሁ የእግዚአብሔር ቃል ከአንደበቱ የማይጠፋ፣ ሁሌም የሚጠቀመው፣ መጽሐፉ ራሱ እሱን ተቆጣጥሮት የአነጋገር ዘዬውን የቀየረውም ሰው ታያለህ። ይህ ሰው የሕጉ መጽሐፍ ከአፉ አልተለየም (ኢያ 1:8)። አበው «ከአነጋገር ይፈረዳል፣ ከአያያዝ ይቀደዳል» እንዲሉ የሚሰማው ሁሉ ማንነቱን ያውቀዋል። «አነጋገርህ ይገልጥሃል» (ማቴ. 26:73)።

ለልጆችህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እየነገርክ ባዩት፣ በሰሙት ነገር ላይ ሁሉ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል እንዲጠቀሙ አስተምራቸው። በመጽሐፍ ላይ፣ በዛፎች ላይ በመሬት ላይ፣ በበር፣ በወንበር፣ በጠረጴዛ፣ በማንኛውም ነገር ላይ ሊሆን ይችላል። ይህን ልምድ አድርጎ ያደገ ልጅ መጽሐፍ ቅዱስ በውስጡ ሕይወት ዘርቶ ይኖራል። ስለዚህ የኃጢአትን ሀሳብ፣ የዓለምን ቋንቋ አያውቅምና እርሱም ኃጢአት አይሠራም። ዳዊትም ያለው ይህንን ነው። «አንተን እንዳልበድል ቃልህን በልቤ ሰወርሁ» (መዝ 118:11)።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት፣ የስሜት፣ የፍቅር፣ የሀሳብ ማዕከል በሆነው ልብህ ውስጥ መቀመጥ አለባቸው። በአፋችን፣ በዕውቀት ማዕከል አእምሮአችን ውስጥ ብቻ መሆን የለበትም። በልብህ ካለ ኃጢአትን ልታደርግ አትችልም። ምክንያቱም ከስሜትና ከሀሳብህ ጋር ተቀላቅሎ ያለው የእግዚአብሔር ቃል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በሉቃስ ወንጌል 2:9



የተጠቀመውን ውብ ቃል ከልብ አስተውለኸዋል? «ማርያም ግን ይህን ነገር ሁሉ በልብዋ እያሰበች ትጠብቀው ነበር።»

እናታችን ሔዋን ደግሞ ሕጉን በአእምሮአቸው (በሕሊናቸው) ሸሽገው፣ በልባቸው ግን ካላኖሩት እና ከበደሉት ሰዎች የመጀመሪያዋ ናት። ስለሕጉ አባብ በጠየቃት ጊዜም መልሷ ትክክለኛ ነበር። ይሁን እንጂ ሕጉን በአንደበቷ እየተናገረችው ፈጣሪዋን ከመበደል አልተመለሰችም። ስለዚህ አንተ ቃሉን በልብህ መዝገብ ልታኖረው፣ ልትጠብቀውና እየተናገርከ ልትሠራው ይገባሃል።

መጽሐፍ ቅዱስህን ዘወትር አንብበው። በየዕለቱ አዲስ ነገርን እያገኘህ እንደሆነ እርግጠኛ ሁን። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል ሀብቱ ሠፊና የማያልቅ ነውና። የማያቋርጥና በቀጥታ ወደእግዚአብሔር ለሚያደርሰው ተመስጦም ምንጩ ነው። «የሥራን ሁሉ ፍጻሜ አየሁ፣ ሕግህ ግን እጅግ ሠፊ ነው።» (መዝ. 118:96) በሰው ዘንድ ለእያንዳንዱ ነገር ወሰንና ገደብ አለው። የእግዚአብሔር ለሆነው ነገር ግን ከጥልቅነቱ የተነሳ ልትወስነው፣ ልትገድበው አትችልም። ይህም የማይወሰነው አምላክ ቃል በመሆኑ ነው። ባሰብከው ባሠላሰልከው መጠን መቆሚያ የሌለውን ስፋቱን ታያለህ። ዘወትር ለአእምሮህ፣ ለመረዳትህ አዲስ ሆኖ የሚቀጥል ነው። ነቢዩ ኤርምያስ ስለዚህ ነገር ሲናገር እንዲህ ይላል። «ቃልህ ተገኝቶአል እኔም በልቼዋለሁ። አቤቱ የሠራዊት አምላክ ሆይ በስምህ ተጠርቻለሁና ቃልህ ሐሴትና የልብ ደስታ ሆነኝ» (ኤር 15:16)

«የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ነው። ነፍስን ይመልሳል። የእግዚአብሔር ምሥክር የታመነ ነው። ሕጻናትን ጠቢባን ያደርጋል። የእግዚአብሔር ሥርዓት ቅን ነው፣ ልብንም ደስ ያሰኛል። የእግዚአብሔር ትእዛዝ ብሩህ ነው፣ ዓይንንም ያበራል...... ከወርቅና ከክቡር ዕንቁ ይልቅ ይወደዳል። ከማርና ከማር ወለላም ይጣፍጣል።» (መዝ 18:7-10)



www.ethiopianorthodox.org

የእግዚአብሔር ቃል ካለው ጥንካሬና ተጽዕኖ የተነሳ፣ አንተ ያነበብከው ማንኛውም ቃል በአንተ ላይ ለውጥ እንደሚያመጣ እርግጠኛ ሁን። ያለብዙ ጥረትና ትግል ቃሉን የተጠማውን ሁሉ ወደጥሩ ሰብእና የመቀየር ኃይል አለው። ቃሉን ስታነበው ያለህ ስሜት እግዚአብሔር ከአንተ ጋር እንዳለና፣ ቃሉ ለመንገድህ ብርሃን እንደሆነ ነው። ቀድሞውኑ ለቃሉ ምንጭ የሆነው መንፈስ ቅዱስ ዛሬም ከግቡ እንዲደርስ ኃይልና ብርታት ይሆነዋል። በጰንጠ ቆስጤ ዕለት ብዙ ሕዝብ በሐዋርያት ሲነገር የነበረውን ቃል ከሰሙ በኋላ «ልባቸው ተነካ..... ወንድሞች ሆይ ምን እንናድርግ? አሉአቸው» የሚለውን እናስታውሳለን (ሐዋ. 2:37) ቅዱስ ጳውሎስም ደቀ መዝሙሩ ጢሞቴዎስን «ከሕጻንነትህ ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን ዐውቀሃል» እያለ ስለመጽሐፍ ቅዱስ ምንነት አበክሮ ሲያስገነዝበው ታነባለህ። (2 ጢሞ. 3:15)። ስለዚህና ከዚህም በላይ ስለሆነው ነገር ሁሉ ነው ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችን ለመጽሐፍ ቅዱስ ታላቅ ክብርና ልዕልና ልትሰጥ የቻለችው።

## መጽሐፍ ቅዱስና ቤተክርስቲያን

ቅድስት ቤተክርስቲያናችን ለመጽሐፍ ቅዱስ ታላቅ ክብር ትሰጣለች። በየዕለቱ በሚቀደሰው ቅዳሴ ላይ ከመጽሐፍ ቅዱስ የወጡ ምዕራፎች ይነበባሉ። ወንጌል ከመነበቡ በፊት የዳዊት መዝሙር በዜማ ይሰማል። ወንጌል እየተነበበ ሳለም ሁለት ዲያቆናት የእግዚአብሔር ሕግ ለእግራችን መብራት ለመንገዳችን ብርሃን ነው የሚል ምሥጢር ያለው የጧፍ መብራት ይዘው ይቆማሉ። ከዚህም በላይ የብርሃናችን ብርሃን የዐይናችን ብርሃን የእግዚአብሔር ቃል ነው ሲሉ ነው። ወንጌሉን ለመስማት በሚደረገው ጸሎትም ካህኑ «እኛንም እንደነርሱ ወንጌልህን ሰምተን ለመሥራት የበቃን ታደርገን ዘንድ በቅዱሳን ጸሎት እንለምንሃን» ይላል። መጀመሪያውኑ ወንጌልን ለመሥማት የበቃን የተዘጋጀን መሆን አለብን። ነገር ግን እኛ በራሳችን የበቃን አይደለንምና የቅዱሳን ጸሎት ያስፈልገናል። ዲያቆኑም «ስለወንጌል ጸልዩ» ብሎ ሲያውጅ ሕዝቡ «ወንጌልህን ለመስማት የተዘጋጀን አድርገን» ይላል። ሕዝቡ



ሁሉ ለወንጌል ከሚሠጠው ክብር የተነሳ ወንጌል ሲነበብ አይቀመጥም። የወንጌሉን ቃል ለዓለም ሁሉ መዳረስ ሲያመለክት ካህኑም ወንጌሉን ከራሱ በላይ ከፍ አድርጎ በመያዝ መንበሩን ይዞራል።

የቤተክርስቲያናችን ስብከት፣ ማንኛውም መንፈሳዊ ትምህርት በሙሉ የተመሠረተው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ነው። ቤተክርስቲያን ለትውፊትም በምትሠጠው ተመሳሳይ ትልቅ ግምት ውስጥም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚጻረር አንዳችም ነገር አይገኝም። ይልቁንም እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በትውፊት የተደገፈ፣ ትውፊትም በመጽሐፍ ቅዱስ መልቶ የሚገኝ ነው እንጂ።

በጸሎተ ቅዳሴም ይሁን በማህበር በምንጸልያቸው ጸሎቶች ሁሉ ውስጥ የምናገኘው በመንፈስ ቅዱስ ያደገውን የመጽሐፍ ቅዱስ ፍሬ ነው። በየሰዓቱ የምንጸልየው ጸሎትም ከዳዊት መዝሙርና ከወንጌል የተወሰደ ስለሆነ ለኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን ጸሎቱ መጽሐፍ ቅዱስን የሚማርበት ሌላው መንገድ ነው።

ቤተክርስቲያን ምሥጢራትን ለመፈጸምም የምትጠቀመው መጽሐፍ ቅዱስን ነው። ለምሳሌ በምሥጢረ ቀንዲል አፈጻጸም ላይ ለሚደረጉት ሰባቱ ጸሎቶች ሰባት የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎች ይነበባሉ። በጥምቀትም ለውሃው በሚደረገው ጸሎት ቡራኬ በርካታ ምዕራፎች ከትንቢት ከመዝሙር፣ ከወንጌልና ከመልእክታት ይነበባሉ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አርአያ በሆነን መሠረት፣ የእግር መተጣጠቡ ሥርዓት በሚፈጸምበት፣ በህማማቱ ሳምንት ሐሙስ ዕለት፣ ህማሙን፣ ሥቃይ፣ መከራውን፣ ትሕትናውን የሚናገሩ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ይነበባሉ። አዲስ የተሠሩ አብያተ ክርስቲያናት ለመባረክ፣ ቤቶችን ለመንፈሳዊ አገልግሎት ለመለየት፣ ሥርዓተ ምንኩስናን ለመፈጸም ቤተክርስቲያን የምትጠቀመው መጽሐፍ ቅዱስን ነው።



www.ethiopianorthodox.org

እውነት ከዚህ በላይ ለመጽሐፍ ቅዱስ መጠንቀቅና ክብር መስጠት ይኖር ይሆን? እስቲ ወደአንተ ልምጣና በሕይወትህ ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ስለሚገኘው የሕይወት ጥቅምና እንዴት ማንበብ እንዳለብህ ብሎም ስለአንተና መጽሐፍ ቅዱስህ ግንኙነት እንነጋገር።

## አንተና መጽሐፍ ቅዱስ

ግንኙነታችሁ በተወሰኑ ዋና ዋና ነጥቦች ላይ የተመሠረተ ነው። ከእነዚህ መካከል እጅግ በጣም ጠቃሚ የሆኑትን ብናነሳ መጽሐፉን የራስ ማድረግ፣ እንደግል ጓደኛ መጠበቅ፣ ማንበብ፣ መረዳት፣ በቃሉ መመሠጥ ናቸው። እንደቃሉ መኖር፣ ትእዛዛቱን በተግባር መተርጎምና ወደሕይወት መቀየርንም ይጨምራል።

## መጽሐፍ ቅዱስን

### 1. የራስህ አድርገው

ወንድሜ ሆይ እንደእውነተኛ ክርስቲያን መጠኑ ከፍ ያለና በጠረጴዛህ ላይ ተቀምጦ ልታነበው ልትማርበት የሚያስችልህ ወይም በመጠኑ አነስተኛ የሆነ በሄድክበት የሚሄድ፣ የማይለይህ መጽሐፍ ቅዱስ ሊኖርህ ግድ ነው። እንደ መልካም ወዳጅ በሄድክበት የሚሄድ፣ በሥራህ ሰዓት አብሮህ የሚሆን፣ በዕረፍትና ከሰዎች ጋር በምትሆንበትም ጊዜ የማይለይህ ጓደኛህ መጽሐፍ ቅዱስ ሊሆን ይገባል። ያለ እርሱ ምንም መሥራት እንደማትችል ይሰማህ። ይህ ቢሆን እንዲያው በአጋጣሚ ዘንግተህ እንኳን ብቻህን ብትወጣ አንድ ወሳኝ ነገር እንደጎደለህ ታስባለህ።

በቤትህና በሕይወትህ መጽሐፍ ቅዱስ እንግዳ እንዳይሆንና ራሱን የሚያስጠጋበት እንዳያጣ እፈራለሁ (ሉቃ 9:58)። ይህ



የሕይወት መጽሐፍ በንባብ ወይም በጸሎት ከፍልህ ራሱን እንዲያስጠጋ አድርገው። ይህን ስልህ ደግሞ እንደ ብርቅዬ ዕቃ፣ ለውበትና ለጌጥ እንደሚደረግ ነገር ዝም ብለህ አስቀምጠው ማለቴ አይደለም። ማለቂያ የሌለውን ጥቅሙን፣ ሥፍር ቁጥር የሌለው ሀብቱን እንድትወርስ ነው እንጂ። መጽሐፍ ቅዱስ የሚመክርህን እያደረግህ፣ ባስተማረህ እየኖርህ የግልህ አድርገው።

### 2. አፍቅረው

መጽሐፍ ቅዱስ አንተን ወሠን በሌለው ፍቅር ከሚያፈቅርህ እግዚአብሔር የመጣልህ መልእክት ነውና አፍቅረው። ከምትወደው ወዳጅህ እንደመጣልህ የእውነተኛ ፍቅር ደብዳቤ ተቀበለው። ይህን ዓይነት ደብዳቤ የደረሠውን ሰው ልብ ብለህ አይተኸዋል? ደጋግሞ ደጋግሞ ያነበዋል። ምክንያቱም ደብዳቤው ለእርሱ እጅግ ውድ የሆኑ ቃላትን የያዘ ነው። ለምንስ ይመስልሃል ነቢዩ ቅዱስ ዳዊት «ከወርቅና ከክቡር ዕንቍ ይልቅ ይወደዳል፣ ከማርና ከማር ወለላም ይጣፍጣል» ያለው? (መዝ. 18:10)

መጽሐፍ ቅዱስን ከልብህ የምታፈቅረው ከሆነ ከማንበብህ ደስታና እርካታ ታገኛለህ። ይህ ማለቂያ የሌለው መንፈሳዊ እርካታ ደግሞ ማንበብህን በጽናት እንድትቀጥልና እንድትመሠጥበት ያደርግሃል።

### 3. በትዕግሥትና ባለመሠልቸት አንብበው

ቅዱስ ዳዊት በመጀመሪያ መዝሙሩ እንደገለጸው መንፈሳዊ ሰው ደስታው በእግዚአብሔር ቃል ነው። በቀን በሌሊት እያሠበው የሚመሠጠው በእግዚአብሔር ቃል ነው (መዝ. 1:2)

ቋሚ በሆነና በማይቆራረጥ መሠረት ላይ የተመሠረተ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ወደር የሌለው ከፍተኛ ጥቅም አለው። በውስጡ ያለው የተቀደሰ መንፈስ እንዲዋሃድህ ከማድረጉም በላይ የሚያመጣው በጎ ተጽእኖና ለውጥም በውስጥህ የጸና ይሆናል። በዚሁ



www.ethiopianorthodox.org

ከቀጠልህ ማንበብህ በራሱ ቅዱስ ልምድ ይሆንልሃል:: ከመጽሐፍ ቅዱስ የተውጣጡ በየዕለቱ ጠዋት ጠዋት፣ ከቤት ከመውጣትህ በፊት የምታነባቸው ክፍለ ንባቦች ይኑሩህ:: በማለዳ ይህን ማድረግህ ቀኑን ሙሉ ሕሊናህን በመግዛት እንድትውል ያስችልሃል:: በመግባትህም በመውጣትህም በውስጥህ የመላው የእግዚአብሔር ቃል ይሆናል:: ከመተኛትህም በፊት ቢያንስ አንድ ምዕራፍ አንብብ:: እንቅልፍ እስከሚወስድህ ጊዜ ድረስ ትመሠጥበትና ከዚያም ሕልምህ የእግዚአብሔር ቃል ይሆናል::

መጽሐፍ ቅዱስ በትዕግሥት፣ ዘወትር ለሚያነበው ሁሉ የደስታ ምንጭ ነው:: ከቃሉም ጋር የተዋሃደ ይሆናል:: ሁሌም በሀሳቡ ውስጥ የሚኖረው የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሆናል:: ስለዚህ ወንድሜ ሆይ በቀን በሌሊት ሕሊናህ በእግዚአብሔር ሕግ የተመሠጠ ልትሆን ትችላለህ:: ይህ ደግሞ በከፍተኛ ኃላፊነት ላይ ለነበረው ንጉሥና ነቢይ ቅዱስ ዳዊት እንዲሁም ታላቅ መሪ ለነበረው ለኢያሱ እንኳን የተቻለ ነበር:: ከዚህ አንጻር ቀለል ባለ የኃላፊነት ሥፍራ ላይ ለምትገኘው ለአንተና ለሌላው እንዴት የተመቸ እንደሆነ አስበው::

## 4. በታላቅ አክብሮት አንብበው

መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ማለት ለአንተ የሚናገረው እግዚአብሔርን መስማት ማለት ነው:: ስለዚህ ስታነበው ተገቢውን ክብር በመስጠት መሆን አለበት:: ለምታነበው ክቡር ቃል በምትሠጠው ክብር መጠን ደግሞ፣ ቃሉ በአንተ የሚያመጣው ለውጥ ይወሠናል:: ለዚህ እኮ ነው ቤተክርስቲያናችን ውስጥ ወንጌል ከመነበቡ በፊት ዲያቆኑ እግዚአብሔርን በመፍራት ተነስታችሁ ቅዱሱን ወንጌል ስሙ (አድምጡ) የሚለን:: ካህኑም ከማንበቡ በፊት ለታላቁ ወንጌል ክብር እጣኑን ያሳርጋል:: «ወንጌልህን ለመስማት እንደሠማነውም ለመሥራት የበቃን የተዘጋጀን አድርገን» እያለ ሕዝቡን ወክሎ ይጸልያል:: ሰው ወንጌልን ለመስማት የመንፈስ ዝግጅት፣ ብቃት ያስፈልገዋል:: ሙሴ ሕዝበ እግዚአብሔር እስራኤልን አሥሩን ሕግጋት ለመሥማት ራሳቸውን እንዲቀድሱ፣



ለሦስት ቀናት ዝግጅት እንዲያደርጉ እና ለክብሩ የበቁ እንዲሆኑ ሲያዘጋጃቸው እንደነበረ እናስታውሳለን:: (ዘጸ 19:10-15)

መጽሐፍ ቅዱስን በግድ የለሽነትና በንቀት የሚያነበው ሰው ቢኖር በቃሉ ሊለወጥ አይችልም:: ይልቁንም ተናጋሪው እግዚአብሔርን ስለናቀ ይፈረድበታል:: ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስህን በታላቅ አክብሮትና በከፍተኛ ትኩረት ማንበብን ልትማር ይገባሃል:: ቤተክርስቲያን ስትሠጠው ያየኸውን ክብር ሁሉ አንተም ለመጽሐፍ ቅዱስ ስጥ::

## 5. በማስተዋል አንብበው

አምላካዊ ወደሆኑት ወደእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ጠልቀህ ግባና ምን እየነገሩህ እንደሆነ መርምረህ ተረዳ:: እንደተራ መጽሐፍ ሳይሆን፣ ሙሉውን ሀሳብህን አስገዝተህ፣ ተመስጠህ አንብበው:: «ጥበበኞቹም እንደሰማይ ጸዳል፣ ብዙ ሰዎችንም ወደጽድቅ የሚመልሱ፣ እንደከዋክብት ለዘለዓለም ይደምቃሉ::» (ዳን. 12:3) ፈሪሳውያን ከአይሁድ መካከል ሊቃውንት የሚባሉ ነበሩ:: ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል መረዳትና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ አልቻሉም ነበር:: ለምሳሌ «የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ» የሚለውን ቃል ይናገሩታል:: ይሁን እንጂ ምን ማለት እንደሆነ አይረዱትም:: ጌታችን ስለደጉ ሳምራዊ እስከነገራቸው ጊዜ ድረስም «ባልንጀራ» ምን ማለት እንደሆነ እንኳ አያውቁም ነበር::

መሠረታዊውና ለንባብ ጉልህ ሚና የሚጫወተው ማስተዋልና መረዳት ነው:: «ሕዝቤ ዕውቀት ከማጣቱ የተነሳ ጠፍቷል» (ሆሴ 4:6) ማስተዋልና ዕውቀት ከሚያስፈልጉባቸው ነገሮች አንዱ፣ አንዲት ጥቅስ ላይ ተመሥርቶ ከመሳት ለመጠበቅ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፈ መጽሐፍ እንጂ የጥቅሶች ክምችት አይደለም:: አንድ ነጠላ ጥቅስ ትክክለኛውን የእግዚአብሔር ዓላማና ትእዛዝ በበቂ ሁኔታ አይገልጽም:: ስለዚህ ከምትፈልገው ርእስ ጋር የሚዛመዱ ብዙ ጥቅሶችን ከነሙሉ ንባባቸው ፈልገህ



www.ethiopianorthodox.org

አሰባሰብ፡፡ በዚህ ነው ትክክለኛውን መልእክት መረዳት የምትችለው፡፡

## 6. የምታነበው ሁሉ በመንፈስና በጥልቀት ይሁን!

በቃሉ ሕሊናህ ሳይሰቀልና ሳትረዳው ከቀረህ ብዙ ማንበብህ ምንም ጥቅም የለውም፡፡ የአንተ ጥቅም የሚወሠነው ወደቃሉ ውስጥ ጠልቀህ በመግባትህ ቃሉም የአንተን ውስጣዊ ስሜት እየበረበረ ሀሳብህን፣ ልብህን፣ ሁለንተናህን መንካትና ተጽእኖ ማሳደር እንዲችል ማድረግ ከመቻልህ ላይ ነው፡፡ ስለዚህ በትክክል የሕጉ (የቃሉ) መንፈስ ምንድን ነው? ብለህ በመንፈስ መርምር፡፡ ደግሞም ቃል በቃል በሚሠጥህ ትርጉም ላይ ብቻ ሳታተኩር፣ ወደውስጡ ግባ፡፡ ጌታችን እንደተናገረው ቃሉ መንፈስና ሕይወት ነው፡፡ (ዮሐ. 6:63)፡፡ ወሳኝ የሆነውን ጥቅሙንም የምታገኘውም በእውነት፣ በመረዳት ውስጥ ባለው በመንፈሳዊ መልእክት ብቻ ነው፡፡ ቃል በቃል የሚተረጎመውንማ ጸሐፍትና ፈሪሳውያንም ይጠቀሙበት አልነበረምን?

ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን ሲገልጽ እንዲህ ይላል «በመንፈስ እንጂ በፊደል ለማይሆን ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንሆን ዘንድ አበቃን ፊደል ይገድላልና መንፈስ ግን ሕይወትን ይሠጣል፡፡» (2 ቆሮ 3:6)

ስለመንፈሳዊነትም ይሁን ስለእምነት ወይም ዶግማ በማስተዋል፣ በመንፈስ ማንበብ እጅግ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ብዙ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ያነቡታል፡፡ ነገር ግን የሚያነቡት ስለማይገባቸውና ትክክለኛውን ትርጉም ስለማይረዱት ሀሳባቸው ይከፋፈላል፡፡ «መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት» የሚለውን አይገነዘቡትም፡፡ (ራዕ 3:6) የክብር ባለቤት ክርስቶስም «መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ» ነው ያለን፡፡ (ማቴ 22:29) ስለዚህ እያንዳንዳቸውን የምታነባቸውን ቃላት ትርጉምና መልእክት ጠልቀህ በመንፈሳዊነት መርምረህ ተረዳ፡፡ መምህራንንም ጠይቅ፣ አማክር፡፡



ብዙ መናፍቃን መጽሐፍ ቅዱስን ያነቡታል፡፡ በአንዳንድ አባኖቻችን ዘንድ እንዲያውም እንደሊቃውንት ይቆጠራሉ፡፡ ነገር ግን ከማስተዋልና ከመረዳት ማነስ ከትክክለኛው መንገድ ስተዋል፡፡ አንዳንዶም ከመጽሐፍ ቅዱስ አንዲት ጥቅስ ይዘው ስለሚነሱና የቀረውን ሙሉ ሀሳብ ስለሚዘነጉት ሙሉ የሆነ መረዳት የላቸውም፡፡ይህን ቃል እንደምሳሌ ውሰድ «ከእኔ አብ ይበልጣል» (ዮሐ 14:28)

ይህን ለመተርጎም ቢፈልጉ እንኳን «እኔና አብ አንድ ነን» (ዮሐ. 10:30) ያለውን ቃል ከግምት ውስጥ አያስገቡትም፡፡

ስለእምነት ለመናገር ሐዋርያው «በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህም ትድናላችሁ» እንዳለ ይጠቅሳሉ (ሐዋ 16:31)፤ ነገር ግን ጌታችን «ያመነ የተጠመቀ ይድናል»ካለው ጋር አያይዘው ሲገልጹት አይታይም፡፡ (ማር 16:16) ፡፡

ስለዚህ ማንም «ተጽፎአል» ብሎ ቢጠቅስብህ እንደጌታችን «ደግሞ ተጽፎአል» ብለህ መልስለት፡፡ አንድ ኃዘንተኛ ሰው «ከፊት ኃዘን የተነሳ ልብ ደስ ይሠኛልና» (መክ 7:3) ቢልህ ደግሞም «በጌታ ደስ ይበላችሁ፣ ደግሜ እላለሁ ደስ ይበላችሁ» የሚል ተጽፎአል ብለህ መልስለት፡፡ (ፊልጵ 4:4) ደግሞም «ለሁሉም ጊዜ አለውና፡፡ ለማልቀስ ጊዜ አለው፣ ለመሳቅም ጊዜ አለው፡፡» የሚል ተጽፎአል (መክ 3:1.4)፡፡ በዚህ መንገድ ብትሄድ ያነበብከውን በማስተዋልና በመረዳት ጠቢብ ትሆናለህ፡፡

አንድ አድቬንቲስት «የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ» (ዘጸ 20:8) የሚለውን ጠቅሶ ቢከራከርህ፣ ደግሞም «እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ ወይም ስለበዓል ስለወር መባቻ ወይም ስለሰንበት ማንም አይፍረድባችሁ፡፡ እነዚህ ሊመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ ናቸውና፡፡» (ቆላስ 2:16) የሚል ተጽፎአል ብለህ መልስለት፡፡

በዚህ መልኩ የተሰባሰቡት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ጽኑ የሆነ ሀሳብንና ጥልቅ የሆነ መረዳትን ይፈጥራሉ፡፡



www.ethiopianorthodox.org

## 7. በቃልህ አጥናው

ይህም ሌላው በአንተና በመጽሐፍ ቅዱስ መካከል ያለው ግንኙነት ነው:: ከመጽሐፍ ቅዱስህ ውስጥ ልዩ መንፈሳዊ መመሪያህ የሚሆኑትን፣ ወይንም መሠረተ እምነት (ዶግማ) የሆኑትን፣ የሚያበረታቱና የሚያጽናኑህን የእግዚአብሔር ቃል ኪዳኖች እና ለችግሮችህ ምላሽ የሆኑትን ቃላት ያለመጽሐፍ በአእምሮህ ውስጥ ቅረጻቸው:: በጣም አሳሳቢ እንደሆኑ ነገሮች በሕሊናህ አሰላስላቸው:: በዚህ ዓይነት ወደነፍስህ ዘልቀው ይገቡና በማስታወስህ ውስጥ ተተክለው በአስፈላጊው ጊዜ ሁሉ የረድኤት የመጽናናት ምንጮች ይሆኑሀል::

ለምሳሌ በዚህ መልክ ማጥናት ትችላለህ::

የተራራው ስብከት ማቴ 5፣ የፍቅር ባህርያት 1 ቆሮ 13፣ በሮሜ 12 እና በ1 ተሰ 5 የሚገኙትን በርካታ ለመንፈሳዊ ሕይወት የሚበጁ ምክሮች፣ ወይም ከመጽሐፈ ምሳሌና መክብብ፣ 10ሩን ትእዛዛት ዘጸ 20 እና ዘዳ 5፣ የዳዊትን ምርጥ መዝሙሮችና ጸሎቶች፣ ስታነባቸው ልብህን የሚነኩትን ሌሎች ጥቅሶች፣ ስለጥሩ ሥነ ምግባር የሚነግሩህን እና የመሳሰሉትን በቃልህ ማጥናት ትችላለህ::

አስበው! አንድ መንፈሳዊ ሰው በቀን አንድ ጥቅስ ቢያጠናና በቃሉ ቢይዝ በአንድ ዓመት ምን ያህል ሊይዝ ይችላል?

ይህም ባይሆን በሳምንት እንኳን አንድ ጥቅስ ቢይዝ፣ ያለጥርጥር በዓመት 52 ጥቅሶች በ10 ዓመት 520 ጥቅሶች በአእምሮው ውስጥ ሊኖሩት ይችላል:: ይህ በጣም በጥቂቱና ሳይጨነቅ ሳይጠበብ የሚያደርገው ሲታሰብ ነው እንጂ እንደዚህ በከንቱ በሚባክነው ወርቃማ ጊዜያችን ምን ያህል የሕይወት ቃላት ልናከማች እንደምንችል ገምት!

ቀጣዩ ደግሞ እነዚህን ቃላት ወደሕይወት መቀየርና ተግባራዊ ማድረግ ነው:: እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰው ቃሉን ሰምቶ የሚያደርገው ነው::



አንተ ወንጌልን አጥናው፣ እርሱ ይጠብቅሃል:: መዝሙሩን አጥናው፣ መዝሙሩም አንተን ይጠብቅሃል:: እንዴት? የሚቀጥለውን ተመልከት

## 8. ሕሊናህን በመግዛት /በመሠብሠብ/ አንብበው::

ከመጽሐፍ ቅዱስህ ውስጥ ያጠናሃቸው ማናቸውም ቃላት ራስን የመግዛት፣ ሕሊናን የመሠብሠብ ምንጭ ሊሆኑህ ይችላሉ:: ቃላቱን ከነፍስህና ከሀሳብህ ጋር ታዋህዳቸውና ቀጥሎ በሚበዛልህ የእግዚአብሔር ጸጋ ውጤቱን ታያለህ:: እያንዳንዱ ቃል ሠፊ ትርጉምና ጠቀሜታ እንደነበረው፣ በየዕለቱ አዲስ ሆኖ በልብህ ውስጥ እንደሚያድግና ፍፁም መንፈሳዊ ሁኔታ ውስጥ የገባህ እንድትሆን የሚያደርግህ መሆኑን ታያለህ:: ስለዚህ እኔ የምመክርህ እንድታነብ ብቻ ሳይሆን፣ ቃሉን እንደሥጋ ፈቃድ እንዳትተረጉመውና በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ሆነህ፣ በመንፈስ መርምረህ እንድትረዳው ነው:: «ይህን በመጀመሪያ ዕወቁ፣ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፣ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ::» (2 ጴጥ 1:20)

በዚህ ጉዳይ ላይ በሠፊው የምንነጋገረው በምዕራፍ ፬ ስለሆነ አሁን ወደሚቀጥለው ነጥብ እንለፍ::

## 9. በጸሎት መንፈስ አንብበው

አምላክህ እግዚአብሔር ማስተዋልን እንዲሠጥህ፣ ፈቃዱን እንዲገልጽልህ በመጸለይ ጀምር:: እንደ ቅዱስ ዳዊት «ዐይኖቼን ክፈት ከሕግህም ተአምራትን አያለሁ» በለው:: (መዝ 118:19):: ስትጨርስም ጌታን ያነበብከውን ተግባራዊ ለማድረግ ጽናቱን እንዲሰጥህ፣ ማስተዋሉንና ተነሳሽነቱን እንዲያድልህ ጌታን በመለመን አጠቃልል:: መጽሐፍ ቅዱስ «በፍጹም ልብህ



www.ethiopianorthodox.org

በእግዚአብሔር ታመን፣ በራስህም ማስተዋል አትደገፍ።» ስለሚልህ ስታነበው በጸሎት የታጀብክ ሁን።
(ምሳ 3:5) ትክክለኛውን አምላካዊ መልእክት በጸሎትህ ለመቀበል ሞክር።

አንዳንድ ሰዎች አስቀድመው የወሡትን ነገር ለማረጋገጥ ሲሉ ብቻ ወይም ያንን የሚደግፍላቸውን ጥቅስ ለማግኘት ያነባሉ። የተገለጸውን የእግዚአብሔር ሀሳብ ወደገዛ ፈቃዳቸው ለመቀየር ይጥራሉ። አንተ ግን ለመረዳትህና እግዚአብሔር የሚልህን ብቻ ለመስማት ተዘጋጅተህ አንብብ። ሃሳብህን ወደእግዚአብሔር ሃሳብ ለመቀየር እንጂ የእግዚአብሔርን ወደአንተ ለመቀየር አታንብብ ትሕትና ለጸሎት እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስን ስታነብ የሚያስፈልግህ ትልቁ ነገርም እርሱ ነው።

በትሕትና ለመጽሐፍ ቅዱስ ቃሎች መታዘዝ ትችላለህ።
ትሕትና ሀሳብህን መቀየር ማረቅ የምትችልበት መንገድ ነው።
ትሕትና ከዳዊት ጋር «አቤቱ መንገድህን አመልክተኝ ፍለጋህንም አስተምረኝ» እያልክ ዕውቀትን እንድትለምን የሚያደርግህ ነው። (መዝ 24:4)።

ሕሊናህ ተሰቅሎ በቃሉ ተመስጠህ ስታነብ
«ጌታ ሆይ ምን አደርግዘንድ ትወዳለህ?» በለው።
በእርግጥ ምን ማድረግ አለብህ? ተከተለኝ።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ኃይልና ውጤቱ

በቤትህ ያለው ቦታና የአንተ ድርሻ

አምላካችን ስሙ የተመሠገነ ይሁንና ይህን በተመለከተ የሚነግረን ግልጽ የሆነ ቃል ይህ ነው። «ከአፌ የሚወጣ ቃሌ እንዲሁ ይሆናል፣ የምሻውን ያደርጋል። የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደእኔ በከንቱ አይመለስም።» (ኢሳ 55:11)።



በትክክል! የእግዚአብሔር ቃል ባዶውን አይመለስም። የራሱ የሆነ ኃይልና ውጤት አለው። ኃያል ቃሉን ሰምተው በሕይወታቸው ተግባራዊ ያደረጉት ሰዎች ኃይሉን ለሌሎችም ማስተላለፍ ችለዋል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የቃሉን ኃይልና ተጽእኖ ሲገልጽ ያለውን ልብ ብለሃል? «የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፣ የሚሠራም ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው። ነፍስንና መንፈስንም— ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል። የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል» (ዕብ 4:12)

«ካልተነካሁበት ለምን አነበዋለሁ?» ብለህ ታስብ ይሆናል። ችግሩ ግን ከምታነበው ቃል ሳይሆን ከአንተ እንደሆነ እርግጠኛ ሁን። ቃሉማ በሁለቱም ወገን የተሳለ ሰይፍ ነው። ይሁን እንጂ ሰይፉ ሥጋን እንጂ ድንጋይን አይቆርጥም። ለዚህ እኮ ነው ጌታ እግዚአብሔር በነቢዩ ሕዝቅኤል አድሮ «የድንጋዩን ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ። የሥጋንም ልብ እሠጣችኋለሁ» ያለው (ሕዝ 36:26) ።

የእግዚአብሔርን ቃል ለመቀበል የአንተ ልብ ምን ዓይነት ነው? ድንጋይ ወይስ አለት ነው? የእግዚአብሔር ቃል ሕያውና ውጤታማ ነው። የበለጠ የሚሠራው ግን ቃሉ እንዲሠራባቸው ፈልገው ልባቸውን ለከፈቱ ብቻ ነው።

የእግዚአብሔር ቃል በአንተ ላይ ዛሬ ባይሠራ ትንሽ ታገስ፣ ነገ ታየዋለህ። ዋናው ነገር ቃሉ በፍጹም በከንቱ አይመለስም። ሁኔታዎች እስከሚመቻቹለትና ልብህ ዝግጁ እስከሚሆን ድረስ በሕሊናህ ውስጥ ጸንቶ ይቆያል። በተወሰነው ሰዓት ግን ውስጥህን ሠርስሮ ሲገባና ውጤታማ ሲሆን ታየዋለህ። የመጀመሪያው ችግር የተፈጠረው ልብህ ስለቀዘቀዘና ፈጣን ምላሽ መስጠት ስላልቻለ ይሆናል። ቀስ በቀስ ግን ራስህ ነቅተህ ትነሳለህ (መኃልይ 5:2-6) ።

«.... ውዶ እጁን በቀዳዳ ሰደደ፣
አንጀቴም ስለእርሱ ታወከ።
ለውዶ እከፍትለት ዘንድ ተነሳሁ፣



www.ethiopianorthodox.org

እጆቼ በደጁ መወርመውሪያ ላይ ከርቤን አፈሰሱ
ጣቶቼ ፈሳሹን ከርቤ አንጠበጠቡ፡፡
ለውዴ ከፈትሁለት ውዴ ግን ፈቀቅ ብሎ አልፎ
ነበር፡፡
ነፍሴ ከቃሉ የተነሳ ደነገጠች.....»

በምድር ላይ የሚዘራው ዘር ሁሉ ወዲያው በቅጽበት ፍሬ አይሰጥም፡፡ ቀናት ወይም ወራት ሊወስድ ይችላል፡፡

እንደዚሁ የእግዚአብሔርን ቃል በልብህ ውስጥ ዝራው፡፡ መልካም ጥንቃቄና ከፍተኛ ጥረት ባደረግህበት፣ ሥራውን ከሚገድብ ውስጣዊና ውጫዊ ችግር በታቀብክበት ጊዜ ላይ አድጎ ፍሬ ይሠጣል፡፡

የእግዚአብሔር ቃል በመሬት ውስጥ ሆኖ ለመብቀል ውሃ እንደሚጠብቅ ዘር ነው፡፡ ዘር ውሃ ሲያገኝ ፈጥኖ ይበቅልና ወጥቶ ይታያል፡፡ ይህን ውብ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ከዚህ ጋር አጣምረህ ተመልከተው፡፡ «እንጀራህን በውሃ ፊት ላይ ጣለው፣ ከብዙ ቀን በኋላ ታገኘዋለህ፡፡» (መክ 11:1)፡፡

እንግዲህ ይህ! ከሆነ ቅጽበታዊ ፍሬዎችን አላየሁም ብለህ በአገልግሎትህ ተስፋ አትቁረጥ፡፡ በመንፈስ ዝለህ እንዳትወድቅ እግዚአብሔርን በትዕግስት ጠብቀው፡፡ ሰዎች ሁሉ አንድ ዓይነት አይደሉም፡፡ ሁሉም ፈጣን ምላሽ አይሰጡም ሁኔታዎችም እኩል የተመቻቹ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ቃሉን ሰምቶ ወዲያውኑ የሚነካበት እንዳለ ሁሉ ቃሉ ለሚፈጥርበት ጥያቄ ብዙ ማብራሪያና አጥጋቢ ትምህርት የሚሻም አለ፡፡ ለሕይወት ሳይሆን ለዕውቀት ብቻ የሚቀበለውም አይጠፋም፡፡ ይህኛው ቃሉን የሚቀበለው ለነፍሱ መዳን ወይም ልቡን ለማንጻት ሳይሆን ዕውቀቱን ለማስፋት ስለፈለገ በአእምሮው ለመያዝ ብቻ ነው፡፡ ልክ በአንድ ሳይንቲስትና በመናኝ ባህታዊ መካከል እንዳለው ልዩነት ማለት ነው፡፡ ሳይንቲስቱ መጽሐፉን ያነባል፣ ያጠናል፣ ያብራራዋል፡፡ እየተናገሩት እንደማያደርጉት ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ይተረጉመዋል፡፡ (ማቴ 23:2)፡፡ ባህታዊው ግን ቅዱስ ዳዊት «አንተን እንዳልበድል ቃልህን



በልቤ ሰወርሁ» እንዳለው እንደትልቅ ሀብቱ ይጠነቀቅለታል፣ ይጨነቅለታል፡፡

## መጽሐፍ ቅዱስ በአንተ ውስጥ የሚሠራው ሥራ

የእግዚአብሔር ቃል በውስጥህ እንዲሠራ ምላሽ በሠጠህበት ጊዜ መለኮታዊው ቃል በውስጥህ እንዲሠራ የምትጠብቀው ነገር ምንድን ነው?
መቼም ውጤቱ እጅግ ብዙ መሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡
እስቲ ጥቂቶቹን አብረን እንመልከት፡-

1. የተበተነውን ሀሳብህን ሰብስቦ ከአምላክህ ጋር ያገናኝሃል፡፡

ሀሳቦችህ የተበታተኑ ከሆኑ በየት እንዳለህ አታውቀውም፡፡ በአጠቃላይ ማንበብ ግን ሕሊናህን ፍጹም አድርጎ በምታነበው መሠረተ ሀሳብ ላይ ብቻ እንድታተኩር ያደርግሃል፡፡ በተለይ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ሰላም ወደሠፈነበት የጸጥታ ወደብ የሚመራህ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ወደእግዚአብሔር የምትጓዝበት መንገድህ ነው፡፡ ንባብህ ክብር የተመላበት ከሆነ ድንቅ የሆነ መሠረታዊ ውጤት ለማየት የምትበቃበትን አትኩሮት ይፈጥርልሃል፡፡

2. አስተዋይና ብሩህ አእምሮ ያለው ሰው ያደርግሃል፡፡

የማስተዋል ብርሃንና ዕውቀትም ይሰጥሃል፡፡

ቅዱስ ዳዊት እንዲህ ይላል «ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴም ብርሃን ነው፡፡» (መዝ 118:105) ደግሞም «የእግዚአብሔር ሥርዓት ቅን ነው፡፡ ልብንም ደስ ያሠኛል፡፡ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ብሩህ ነው፣ ዐይንንም ያበራል» ሲል ታገኘዋለህ፡፡ (መዝ 18:8)፡፡

ወንጌል በሚነበብበት ጊዜ ግድ የምናበራበት ምስጢርም ይህ ነው፡፡ ማንም ሊያስተምርህ ከሚችለው በላይ አስተዋይ የሚያደርግህ



www.ethiopianorthodox.org

መጽሐፍ ቅዱስ ነውና ምስክሩ ትዝታህ ይሁን:: ይህን ብታደርግ የጌታን መንገድና እንዴት ጥበብን ማግኘት እንደምትችል ታውቃለህ:: በተለይ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅዱሳን እንዴት ሠርተው እንዳለፉና እንዴት ከእግዚአብሔር ጋር እንደኖሩ የማወቅ ፍላጎት ካለህ ሀብትህ እጥፍ ድርብ ነው:: «የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ፣ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው::» (ዕብ 13:7)

3. ወደትክክለኛው እምነት ይመራሃል::

ይህ ሊሆን የሚችለው በማስተዋል፣ መለየት በመቻልና በመሪ የምታነብ ከሆነ ብቻ ነው:: ለእያንዳንዱ የምታምንበት ነገር ሁሉ ጥርት አድርገህ የምታውቀው አንድ ወይም ከአንድ በላይ ጥቅስ ከነሙሉ ሀሳቡ አጥንተህ ብትዘጋጅ ከሀሰት ትምህርቶችና ከመናፍቃን የሚጠብቁህ መሳሪያዎች ይሆናሉ:: ይህ ደግሞ ታላላቅ የሃይማኖት አርበኞችና የእምነት ጀግኖች ቅዱሳን የተጠቀሙበት፣ ወደእግዚአብሔር የተጓዙበት መንገድ ነው:: በማስተዋላቸውና ድንቅና ጥልቅ በሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀታቸው ከሀድያንንና መናፍቃንን መቋቋም እንደቻሉ ዕወቅ::

4. ወደንስሐ ሕይወትና ወደመንፈሳዊ እድገት ያደርስሃል::

ድክመትና ኃጢአትህን ባለመሸፈን በትክክለኛው መንገድ ለራስህ የምትሠጠው ግምት ላይ መድረስ የምትችለው በዚህ ውድና ብርቅ መጽሐፍ ሕግጋት ብርሃንነት ነው:: የቅድስና ሕይወትና ፍጹምነት እንጂ ከኃጢአት መመለስ ብቻ እንደማይበቃህ የሚያሳውቅህ ይህ መጽሐፍ ነው:: እነዚህን ሁሉ የእግዚአብሔር ፈቃዶች የነገረህ ማነው? «እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ፣ ተብሎ እንደተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ» (1 ጴጥ 1:15-16፤ ዘሌ 11:44) :: እምላክህ ክርስቶስም «የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተም ፍጹማን



ሁኑ» እያለ ሲመክርህ የምታገኘው በሌላ ሳይሆን በዚህ የሕይወት መጽሐፍ ብቻ ነው:: (ማቴ 5:48)::

መጽሐፍ ቅዱስ ስለንስሐ ሕይወት፣ ቅድስናና ፍጹምነት በምሳሌ የተደገፈ በርካታ ዝርዝር መግለጫዎችን ይሠጥሃል:: ባለማወቅህ እንዳትስትም ያስጠነቅቅሃል:: (ማቴ 22:29)::

5. በኃጢአት ፈተና ውስጥ ብትሆን የአእምሮና የፈቃድ ትሕትናን ያስተምርሃል::

በምታነብበት ጊዜ በመንፈሳዊነትና በእግዚአብሔር ቃል የተቀደሰው ሀሳብህ በቀላሉ በኃጢአት ሊረክስ አይችልም:: ይሁን እንጂ በተዘናጋህበት ጊዜ ላይ ጠላትህ አግኝቶህ እንዳይማርከህ እንዴ ተቀድሼአለሁ እንዳትል፣ መጠንቀቅ እንዳለብህ ሳልመክርህ አላልፍም:: «በመጠን ኑሩ ንቁም! ባለጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራልና:: (1 ጴጥ 5:8)::

6. በዲያብሎስ ውጊያዎች ውስጥ ብትሆን ኃጢአትን በሕግ እንድትመልስ ያስችልሃል::

አንድ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን አባት በመጽሐፉ ስለሀሳብ ውጊያዎች እንደገለጸው ከምንም በላይ ክቡር የሆነው ጊዜህ በከንቱ ልፍለፋና ብዙ በማውራት ቢባክንብህ «በቃል ብዛት ውስጥ ኃጢአት ሳይኖር አይቀርም» የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል አስታውስ:: (ምሳ. 10:19)

መዝሙረኛው ቅዱስ ዳዊትም «አቤቱ ለአፌ ጠባቂ አኑር፣ የከንፈሮቼንም መዝጊያ ጠብቅ» ይላል:: (መዝ 140:3)

ዲያብሎስ ቁጡ፣ ብስጩ እንድትሆን ቢፈታተንህ «ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ፣ ለቁጣም የዘገየ ይሁን:: የሰው ቁጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አይሠራምና» የሚለው የሐዋርያው ያዕቆብ መልእክት (ያዕ 1:19) እንዲሁም «ከቁጡ ሰው



www.ethiopianorthodox.org

ጋር ባልንጀራ አትሁን፣ ከወፈፍተኛም ጋር አትሂድ» የሚለው የጠቢቡ ሰሎሞን ምክር ትዝ ይበልህ (ምሳ 22:24)::

በተመሳሳይ መልኩ በዝሙት ሀሳቦች ቢዋጋህ የልዑሉን ጌታ ትምህርት አስብ:: «ወደሴት ያየ ሁሉ የተመኘትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል::» (ማቴ 5:28):: «ከዐይኔ ጋር ቃል ኪዳን ገባሁ:: እንግዲህስ ቆንጆይቱን እንዴት እመለከታለሁ?» ያለውን ጻድቅ ኢዮብን አትርሳው:: (ኢዮ 31:1) ጠላትህ በአንተ ላይ ያዘጋጀውን ማንኛውም መንፈሳዊ ውጊያ መመለስ የምትችለው የመጽሐፍ ቅዱስን ቃላት ማስተዋልና ሁሌም መጠቀም ስትችል ብቻ ነው:: ሕጉን ማስታወስ ከቻልክ ኃጢአትን ከመፈጸም ትጠበቃለህ:: ኃጢአትን የሠራ ማንም ሰው በአብዛኛው ምክንያቱ ሊሆን የሚችለው ሕግን መርሳቱ ነው:: ኃጢአትን መውደድ ሕሊናን ያደነቁራልና::

7. በጭንቀት ጊዜ መጽናናትን በድካም ጊዜ ብርታትን ይሰጥሃል::

ይህ ቅዱስ ዳዊት በተደጋጋሚ አምላኩን ሲማጸንበት የነበረ ታላቅ ነገር ነው:: «ነፍሴ መድኃኒትህን ናፈቀች፣ በቃልህ ታመንሁ» (መዝ 118:81)፤ ለባሪያህ ተስፋ ያስደረግኸውን ቃልህን አስብ፣ ቃልህ ሕያው አድርጎኛልና ይህች በመከራዬ ደስ አሠኝችኝ» (መዝ 118:49):: በፈተና ውስጥ ሳለ እንኳን ይል የነበረው ይህንን ነው::«እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባይሆን፣ ሰዎች በእኛ ላይ በተነሱ ጊዜ፣ ቁጣቸው በላያችን በነደደ ጊዜ፣ በዚያን ጊዜ ሕያዋን ሳለን በዋጡን ነበር::....ነፍሳችን እንደወፍ ከአዳኞች ወጥመድ አመለጠች:: ወጥመድ ተሰበረ፣ እኛም አመለጥን:: ረድኤታችን ሰማይና ምድርን በሠራ በእግዚአብሔር ስም ነው::» (መዝ 123:2-8)::

ስለተስፋ የሚነግረን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እንዴት ብዙ ነው!

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው እነዚህን ቃላት አንብቦ በልቡ የሚጠብቃቸው፣ ሰላምን አግኝቶ፣ ዘወትር የተጽናና ይሆናል:: «በተስፋ ደስ ይበላችሁ!» (ሮሜ 12:12)::



በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የምታነባቸው የእግዚአብሔር ቃል ኪዳኖች ለውሳሜዊት ነፍስህ ሰላምና ጸጥታን የሚያጎናፅፉህ ናቸው:: «እኔ እስከዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ::» (ማቴ 28:20)::

ይህን የመሳሰሉ መጽናኛዎችህ እጅግ ብዙ ናቸው:: እነዚህን ብታጠናስ? «የእናንተስ የራሳችሁ ጸጉር ሁሉ እንኳን ተቆጥሮአል፣ እንግዲህ አትፍሩ» (ማቴ 10:30)

«እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፣ ማንም ክፉ ሊያደርግብህ የሚነሳብህ የለምና አትፍራ» (ሐዋ 18:10)

ስለነዚህ ሁሉ እንዳልተርከልህ ጊዜና ቦታ ያጥረኛል::

8. ለማንኛውም (ለሁሉም)

መጽሐፍ ቅዱስ፣ ለሁሉም ሰው፣ ለሁሉም ሁኔታዎች፣ ለሁሉም ቦታ ሁሉንም ነገር ይዞ ይገኛል:: በየትኛውም ቦታ ሁን፣ በየትኛውም የሥነ ልቡና ሁኔታ ሁን፣ መጽሐፍ ቅዱስ የምትፅናናበትን ቃል ይሰጥሃል:: የምትፈልገውን፣ አንተን የሚያረካህን ሁሉ ታገኝበታለህ:: ለምሳሌ የዳዊትን መዝሙሮች ብትወስድ ሁሉንም ሀሳቦችና የጸሎት ዓይነቶች ያሳይሃል:: መጽሐፈ ምሳሌም ከምክር ዓይነቶች የሚቀረው አንድም የለም:: አንተ ከመረጥከውና ከወደድከው እያንዳንዱ መጽሐፍ ለአንተ የሚሆን ልዩ መልእክት የያዘ ነው::



www.ethiopianorthodox.org

## መጽሐፍ ቅዱስን

1. ለጸሎት ልትጠቀምበት ትችላለህ

ማንበብ ስትጀምርና ስትጨርስ ጸሎት አድርግ። በተጨማሪም ማንበብህ በውስጥህ ወደጸሎት ልትቀይራቸው የምትፈልጋቸውን ልዩ ሀሳቦች ያቀጣጥልልሃል። ለምሳሌ የዳዊት መዝሙር እንዴት መጸለይ እንዳለብህና በምን ዓይነት ሁኔታ ከአምላክህ ጋር መነጋገር እንደሚገባህ ያስተምርሃል። በተመሳሳይ መልኩ በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ የምታገኛቸው የእግዚአብሔር ሰዎችን ጸሎት ስታነብ ልትማር የምትችለው ነገር እጅግ ብዙ ነው። ከእነዚህም መካከል የነቢዩ ዳንኤል ጸሎት (ዳን 9)፣ የእዝራ ጸሎት (እዝ 9)፣ የናሆም ጸሎት (ናሆ 1)፣ የንጉሥ ሰሎሞን ጸሎት (1 ነገ 8)፣ የዮናስ ጸሎት (ዮናስ 2) እና የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጸሎት (ሉቃ 1) ናቸው።

2. የተመሰጠ ምንጭ አድርገው

ታሪካዊ ከሆኑት መጻሕፍት አንዱን የተለየ ድርጊት መርጠህ በተደረጉት ተዓምራት ላይ ልብና ሀሳብህን ሰቅለህ ተመስጠ አድርግበት።

3. ለመንፈሳዊ እድገት መለማመጃ አድርገው

በሥነ ምግባራዊ ሕይወት ለማደግ እንድትችል አሁን ላለህበት መንፈሳዊ ደረጃና ፍላጎት የሚስማማህ ምን እንደሆነ ምረጥ። መንፈሳዊ ልምምዶች በሚለው ምዕራፍ (በክፍል ሁለት መጽሐፍ) ስለዚህ ጉዳይ ሰፊ መግለጫ ታገኛለህ።

4. የንስሐ መንገድ አድርገው።

በምታነበው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ሁሉ ንስሐ የመግባት ዕድል እንዲኖርህ «ለእኔ» ብለህ አንብበው። ጌታችንም ዮሐንስም «ንስሐ ግቡ» ያሉት ለአንተም እንደሆነ አስብ። ለምሳሌ ጌታችን «እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ። አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ» ያለውን ቃል ብታነብ በውስጥህ የበደልከውን ወይም የበደለህን እንድትታረቅ፣ ይቅር እንድትል፣ ይቅርታም እንድትጠይቅ የሚገፋህ ጠንካራ ኃይልን ስለምታገኝበት ተጠቀምበት። (ማቴ 5፡23)።



## ቤትህ፣ ቤተሰብህና መጽሐፍ ቅዱስ።

በኦሪት ዘዳግም ላይ በተጻፈው በዚህ ትእዛዝ ተነስቼ የማስገነዝብህ ነገር አለኝ። «እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ ለልጆችህም አስተምረው። በቤትህም ስትቀመጥ፣ በመንገድም ስትሄድ፣ ስትተኛም ስትነሳም፣ ተጫወተው። በእጅህም ምልክት አድርገህ እሠረው። በቤትህም መቃኖች በደጃፍህም በሮች ላይ ጻፈው።»
(ዘጸ 6፡6-9)።

እነዚህን ትእዛዛት ምን ያህል ትፈጽማቸዋለህ?

ሀ. ሚስትህ ልጆችህ ሁሌ ሊያስታውሱት የሚችሉት ሕግ በቤትህ ግርግዳ ላይ ተሠቅሏል?

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ እንደተናገረው በልብህ የያዝከውን ለልጆችህ ታስተምራቸዋለህ? «ለልጆችህም አስተምረው።» ልጆችህን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ላይ ብቻ ጥለህ ራስህን ከኃላፊነት ነጻ ታደርግ ይሆን?

መ. መጽሐፍ ቅዱስን በትእዛዙ መሠረት በቤትህ ውስጥ የሚነገር ቋንቋ አድርገህ ትጠቀምበታለህ? «በቤትህ ስትቀመጥ.....ተጫወተው»

ሠ. በየዕለቱ ከቤተሰብህ ጋር ታነበዋለህ?
በመጽሐፍ ቅዱስ ዙሪያ የተሰበሰበ ቤተሰብ አለህ?

ረ. ለልጆችህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን የመያዝ ውድድር አዘጋጅተህ በዚሁ መሠረት ታሠለጥናቸዋለህ?

እኔ በእግዚአብሔር ፊት የጠየቅሁህን ሁሉ ራስህን ጠይቅ!



አዘጋጅ:- ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ

ተርጓሚ
ዲያቆን ግርማ ባቱ
በቅድሥት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ
የ3ኛ ዓመት የዲግሪ ተማሪ

www.ethiopianorthodox.org